የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: የካቲት 02 2015

ቁጥር/REF NO: 9/256/987/15

ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች

ለሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ:- **የሬሚዲያል ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ሰነድ ስለመላክ**

በ2015 የትምህርት ዘመን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚሰጠው የሬሚዲያል ፕሮግራም ትግበራ የተዘጋጀውን የማስፈጸሚያ ሰነድ 13 (አስራ ሶስት) ገፅ አባሪ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኢባ ሚጀና (ዶ/ር)
የአካዳሚክ ጉዳዮች ዋና
ስራ አስፈፃሚ

**ግልባጭ**:-

- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ

  **ትምህርት ሚኒስቴር**

# በ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን አገር አቀፍ የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ወስደው የማለፊያ ውጤት ያላመጡ ተማሪዎች የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ሰነድ

ጥር/ 2015 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

ማውጫ


1. መግቢያ ............................................................. 3
2. አስፈላጊነት ............................................................. 4
3. ግብ ............................................................. 4
4. ዓላማዎች ............................................................. 5
5. የፕሮግራም መግቢያ መቁረጫ ነጥብ ............................................................. 5
6. ተጠቃሚ ተማሪዎች ብዛት ............................................................. 5
7. የምደባ ሁኔታ/ አመዳደብ ............................................................. 5
8. ፕሮግራሙ (ኮርሱ) የሚሰጥበት ቦታ ............................................................. 6
9. ትኩረት የሚደረግባቸዉ ትምህርት ዓይነቶች ............................................................. 6
10. ትኩረት የሚደረግባቸዉ ትምህርት ዓይነት ይዘቶች ............................................................. 6
11. የመማር ማስተማር ዘዴ ............................................................. 6
12. የምዘና ሁኔታ/ዘዴ ............................................................. 7
13. የፕሮግራሙ ርዝማኔ ............................................................. 7
14. የኮርስ ክለሳ አሰጣጥ የጊዜ ርዝማኔ ............................................................. 8
15. ግብአት ( ፋይናንስ፣ የሰው ኃይል እና ቁሳቁስ) ............................................................. 8
16. የወጪ መጋራት ............................................................. 8
17. የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ............................................................. 9
18. የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ............................................................. 12
19. የፕሮግራሙ ማጠቃለያ ፈተና ............................................................. 13
20. የተፈፃሚነት ወሰን ............................................................. 13

የድርጊት መርሃ ግብር ............................................................. 13

## 1. መግቢያ

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር በሀገሪቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እተባባሰ የመጣውን የትምህርት ጥራት ችግር እና በትምህርት ዘርፉ የተስተዋለውን ስብራት ለመጠገን በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል በሃገሪቱ የሚሰጠውን የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና እስከ አሁን ሲሰጥበት የነበረውን አካሄድ በመቀየር የፈተናው ዝግጅት ከምንጊዜውም በላይ በልዩ ጥንቃቄ እንዲዘጋጅ ከማድረግ ጎን ለጎን ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ ሁኔታ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በፈተና ማዕከልነት እንዲያገለግሉ በመወሰን ሁሉም ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲዎች የፈተና ማዕከላት በልዩ ጥንቃቄ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት በ2014 ዓ.ም በተሰጠው የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ለፈተናው ቀርበው ከነበሩትና ፈተናውን ከተፈተኑት 908,256 ተማሪዎች ውስጥ 29,909 ተማሪዎች ብቻ ከ 50 ፐርሰንት በላይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ይህ ወጤት በፈተናው ማለፍ ካለባቸውና ከሚጠበቀው ውጤት አንፃር ሲታይ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ለውጤቱ ዝቅተኛ መሆን እንደምክንያት የሚነሱ ጉዳዮች ዘርፈ ብዙ እና ለወደፊት ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊሰራባቸው የሚገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የፈተና አሰጣጥ ስርዓቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተተገበረ እና የነበረውን ለኩረጃ የሚያጋልጥ የፈተና አሰጣጥ ችግሮችን ያመላከተም ነው፡፡ የተመዘገበው ውጤትም በጥቅሉ ሲታይ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያላቸውን የመቀበል አቅም እንኳን ለመሸፈን እጅግ በጣም ያነሰ እና 19.54 ፐርሰንቱን ብቻ የሚሸፍን ነው፡፡

በመሆኑም የውጤቱ መቀነስ በተማሪዎች፣ በወላጆች፣ በመምህራን፣ በትምህርት ዘርፉ እና በአጠቃላይ በሀገር ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዲሁም ተዛማጅ ችግሮችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችል ስትራቴጅ ማዘጋጀት በማስፈለጉ የትምህርት ሚኒስቴር ለዚህ አመት ብቻ የሚያገለግል ስልት ቀይሶ እየሰራ ይገኛል፡፡ የችግሩን ጉዳት ለመቀነስ የማለፊያ ነጥብ ካላስመዘገቡ ተማሪዎች መካከል በአንፃራዊነት የተሻለ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለ4/አራት/ ወራት ያህል የሚቆይ የማካካሻ ትምህርት በተመረጡ የትምህርት አይነቶችና ይዘቶቻቸው ላይ በማስተማር እና እንደገና ፈተና በመስጠት ተፈትነው የሚያልፉትን ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ እንደ መፍትሄ ተወስዷል፡፡

## 2. አስፈላጊነት

ይህን የማካካሻ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ከሆነባቸው ምክንያቶች መካከል በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ተፈትነው የማለፊያ ነጥብ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ ለመሆኑ በቀጣይ በጥናት የሚረጋገጡ ልዩ ልዩ መንስኤዎች ከመኖራቸው ባሻገር ለተለያዩ አባባሽ ችግሮች መነሻ እንዳይሆን መከላከል ዋነኛው ሲሆን የሚከተሉት ጉዳዮች የማካካሻ ትምህርቱን መስጠት አስፈላጊ የሆነባቸው ምክንያቶች ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1. የፈተና አሰጣጥ ስልቱ አዲስና ለመጀመሪያ ጊዜ የተተገበረ በመሆኑ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተፅኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣
2. የማለፊያ ነጥብ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ አነስተኛ በመሆኑ የዩኒቨርስቲዎች የመቀበል አቅም ማለፊያ ነጥብ ካስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር አንፃር ሲታይ እጅግ የተራራቀ በመሆኑ፣
3. የማለፊያ ነጥብ ያላስመዘገቡ/ ሃምሳ ፐርሰንት በታች ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን በቀጥታ ወደ ዩኒቨርሲቲ ማስገባት እየተሰራበት ያለውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ስራን ስለሚጎዳና ወደ ነበረው አስተሳሰብ የመመለስ አዝማሚያ ስለሆነ፣
4. ተማሪዎቹን ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት እድል ማሳጣት በተማሪ፣ በቤተሰብ፣ በመምህራን፣ በማህበረሰብና በሀገር ላይ ሊያስከትል የሚችለውን የሥነ ልቦና ተፅዕኖ መቀነስ አስፈላጊ ስለሆነ፣
5. የትምህርት ጥራቱን መውደቅና ስብራቱን የማከም ስራ እንዳይቀለበስ ሚዛናዊ እና ምክንያታዊ የሆነ ችግር አፈታት ስልትን መከተል አስፈላጊ በመሆኑ፣
6. በአንጻራዊነት የተሻለ የመማር አቅም እያላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ተደናቅፈው ዝቅተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች ዳግም እድል መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ እና
7. በአጠቃላይ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊደርስ የሚችለውን ኪሳራ መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህን የማካካሻ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

## 3. ግብ

የዚህ ስትራቴጂክ እቅድ ግብ በትምህርት ዘመኑ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግባት ያለባቸውን ተማሪዎች በራሳቸው ጥረትና አቅም እንዲገቡ ማድረግ እና በቀጣይ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ለሚሰሩ ስራዎች መሰረት መጣል ነው፡፡

## 4. ዓላማዎች

1. ሀገራዊውን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ በማሳደግ የመንግስት ፖሊሲ አፈጻጸምን ማሻሻል፤
2. ተማሪዎች የማካካሻ ትምህርት አግኝተው በራሳቸው የግል ጥረት የዩኒቨርሲቲ መግቢያ አቅም እንዲያጎለብቱ ማስቻል፣
3. የመማር አቅም እያላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ተደናቅፈው የማለፊያ ነጥብ ያላስመዘገቡ ተማሪዎች እድል መስጠትና ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
4. በተማሪዎች ውጤት ማነስ ምክንያት በየደረጃው ሊከሰቱ የሚችሉ ተፅዕኖዎች እና አላስፈላጊ ሁከቶችን መከላከል፡፡

## 5. የፕሮግራም መግቢያ መቁረጫ ነጥብ

በፕሮግራሙ የሚካተቱት ተማሪዎች የውጤት መቁረጫ ነጥብ ወደ መንግስት ተቋማት የሚመደቡ ተማሪዎች ምርጫ እና በተቋማት የተከለሰ የቅበላ አቅም ታሳቢ በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 6. ተጠቃሚ ተማሪዎች ብዛት

በፕሮግራሙ የሚታቀፉ ተማሪዎች ብዛት የዩኒቨርሲቲዎችን የመቀበል አቅም ባገናዘበ ሁኔታ በፕሮግራሙ የሚታቀፉ ሲሆን በየተቋማት የሚመደቡ ተማሪዎች ብዛት በዩኒቨርሲቲዎቹ የመቀበል አቅምን መሰረት አድርጎ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 7. የምደባ ሁኔታ/ አመዳደብ

ተማሪዎች ምደባ የሚካሄደው በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት የዩኒቨርሲቲዎችን የመቀበል አቅም መሰረት ባደረገ መልኩ ይሆናል፡፡ ዕድሉን ያገኙ ተማሪዎች በየአቅራቢያቸው በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የሚመደቡ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ የሚወስዱትን አጠቃላይ ፈተና ካለፉ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ በቆዩበት የመንግስት ተቋም ትምህርታቸውን መቀጠል ይችላሉ፡፡

የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሬሚዲያል ፕሮግራም ለመከታተል የሚመዘገቡ ተማሪዎችን ሙሉ መረጃ ( ስም፣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስም፣ አድሚሽን ቁጥር፣



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት ወዘተ...) በማጠናቀር በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን እንዲሁም ለትምህርት ሚኒስቴር ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

## 8. ፕሮግራሙ (ኮርሱ) የሚሰጥበት ቦታ

ለዚሁ የውጤት ማሻሻያ ፕሮግራም የተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች ወይም ለፕሮግራሙ መግቢያ መስፈርት አሟልተው ፕሮግራሙን በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መከታተል ለሚፈልጉ ተማሪዎች የኮርስ ክለሳ መርሀ ግብሩ በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

## 9. ትኩረት የሚደረግባቸዉ ትምህርት ዓይነቶች

የማሻሻያ ትምህርት ትኩረት የሚደረግባቸው ትምህርት (ኮርስ) ዓይነቶች ለተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ሂሳብ፣ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ፊዝክስ እና እንግሊዝኛ ሲሆን ለማህበራዊ ሳይንስ ሂሳብ፣ እንግሊዝኛ፣ጅኦግራፊ እና የታሪክ ኮርሶች ይሆናሉ፡፡

## 10. ትኩረት የሚደረግባቸዉ ትምህርት ዓይነት ይዘቶች

የሬሚዲያል ፕሮግራሙ የማህበራዊ ሳይንስ እና ተፈጥሮ ሳይንስ መስክ ተከፍሎ በማእክል በተዘጋጀ ይዝት መሰረት ዩኒቨርሲቲዎች በተጨማሪ የሚያክሉትን በማካተት ፕሮግራሙ በተዘጋጀው መነሻ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 11.የመማር ማስተማር ዘዴ

እነዚህ የማለፊያ ውጤት ያላመጡ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ውስጥ ሲማሩ የነበሩትን ትምህርት ወይም ኮርስ መልሰው በሞጁል መልክ የሚወስዱ ሲሆን ምንም መሰረታዊ እውቀት እንደሌላቸው ተደርገው አይቆጠሩም፡፡ በመሆኑም ፍጹም ለመደበኛው 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከጫፍ እስከ ጫፍ ሁሉንም የትምህርት ይዘቶች ማስተማር ከብዙ ሁኔታዎች አንጻር ሲታይ አዋጭ ስለማይሆን እንደ ዩኒቨርሲቲ ተማሪም በሌክቸር መልክ ማስተማሩ ተማሪዎቹን አሁን ከሚኖርባቸው የስነ ልቦና ጫና አንጻር ይህ ዘዴም በሚፈለገው ደረጃ ሳያበቃቸው ይችላል፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

በመሆኑም በተማሪዎቹ ላይ የመማር ፍላጎትን የሚያሳድር፣ በራስ እና በቡድን የመማር ልምድን የሚያሳድግ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በአግባቡ የመጠቀም ልምድን፣ የቤተ-መጻሕፍት አጠቃቀም ልምድን እና በአጠቃላይ የማንበብ ባህልን የሚያሳድግ አቀራርብ የተከተለ የመማር-ማስተማር ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

## 12. የምዘና ሁኔታ/ዘዴ

የማካካሻ ትምህርት መርሀ-ግብሩ ተጠቃሚ ተማሪዎች በሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነቶች ይዘት ላይ ተገቢውን ዕውቀት መጨበጣቸውን የሚያረጋግጥ የምዘና ስልት የሚተገበር ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ምን ያህል ተምረዋል የሚለውን ለመመዘን ወይም ለማወቅ እና ተማሪዎች በትጋት እንዲማሩ የሚያበረታታ እና የመማር ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ድጋፍ ለማድረግ በሚያስችል አግባብ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የማካካሻ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ተማሪዎች ተከታታይ ምዘና እንዲኖራቸው ተደርጎ በየተቋማቱ የሚሰጠው ምዘና ሰላሳ ፐርሰንት (30%) እና በማእከል ተዘጋጅቶ የሚሰጠው ፈተና ሰባ ፐርሰንት (70%) የሚሸፍን ይሆናል፡፡ በሁለቱ ድምር አማካይና ከዚያ በላይ (50 በመቶና በላይ) የሚያመጡ ተማሪዎች በመንግስት ተቋማት ትምህርቸውን ሲከታተሉ በቆዩበት በዚያው ተቋም ትምህርታቸውን መቀጠል የሚችሉ ሲሆን በራሳቸው ወጪያቸውን ሸፍነው ወደ ግል ተቋማት ሄደው መማር ቢፈልጉ ወደ የሚፈልጉት የግል ተቋም ሄደው የመማር መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል፡፡

## 13. የፕሮግራሙ ርዝማኔ

ምንም እንኳን ኮርሶችን በመከለስ ተማሪዎቹን በማገዝ የምዘና ውጤታቸው እንዲሻሻልና ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚችሉ ተማሪዎችን ቁጥር ለማሳደግ የተለያዩ ጥረቶች የሚደረጉ ቢሆንም እነዚህ ጥረቶች በጊዜ የተገደቡ ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም የሚከለሱ ኮርሶች ለተፈጥሮ እና ለማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ ተማሪዎች ተብለው በተመረጡ ኮርሶች ላይ ብቻ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ተማሪዎች አስቀድመው የተማሩት ኮርሶች እና ፕሮግራሙ የክለሳ ፕሮግራም ስለሆነ ፕሮግራሙ ረጅም ጊዜ መፍጀት የለበትም፡፡ ይህንኑ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የነዚህ የኮርስ ማካካሻ ፕሮግራም ለአራት (4) ወራት ከየካቲት 15 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ይሆናል፡፡

## 14. የኮርስ ክለሳ አሰጣጥ የጊዜ ርዝማኔ

ለክለሳ የሚመረጡ ኮርሶች እና የኮርሶቹ ይዘት እንደየ ትምህርት መስኩ የሚለያዩ ይሆናል። ስለሆነም ወጥ የሆነ የኮርስ ክለሳ የጊዜ እርዝማኔ አይኖርም። ሆኖም ግን አንድ ኮርስ ወይም ለዚህ ተብሎ የሚዘጋጀው ሞጁል ቢበዛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል።

## 15. ግብአት ( ፋይናነስ፣ የሰው ኃይል እና ቁሳቁስ)

### ሀ. ፋይናንስ

ለማካካሻ ትምህርት ለሚመደቡ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው መደበኛ በጀት ከሚመደበው ለትምህርትና ተያያዥ ወጪዎች እንደ ማንኛውም መደበኛ ተማሪ ወጪ ስርዓት የሚከናወን ይሆናል።

### ለ. የሰው ኃይል

ሁሉንም የሰው ኃይል አስተዳደርና ስምሪት በዩኒቨርሲው አሰራር የተከተለ ሆኖ በዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር እና በትምህርት ሚኒስቴር እና በዩኒቨርሲቲዎች የሚቋቋማው ግብረ ሃይል የጥብቅ ክትትል የሚመራ ይሆናል።

### ሐ. ቁሳቁስ

ለትምህርቱ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቁሳቁች እንደማንኛውም ጊዜ በዩኒቨርሲቲዎች የሚሸፈን ሆኖ የማስተማሪያ ሞጁልን በተመለከተ ከትምህርት ሚኒስቴር የሚሰራጭ ይሆናል።

## 16. የወጪ መጋራት

የመካካሻ ትምህርታቸውን አጠናቀው ፈተና አልፈው ወደ አንደኛ አመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች በቆይታቸው ጊዜ በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት አሰራር መሰረት የአንድ ሴምስቴር ክፍያ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ሲገቡ ተጨማሪ ውል

## 17. የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### ሀ. የትምህርት ሚኒስቴር

1. ፕሮግራሙን የሚመራ ግበረ-ኃይል ያቋቁማል፤
2. ፕሮግራሙ የሚመራበትን የፕሮግራሙን ማስፈጸሚያ ሰነድ/መመሪያ ያዘጋጃል፤
3. ከተማሪ ቅድመ ምደባ እና በምደባ ወቅት እና ከምደባ በኂላ ሂደቶቹን በሙሉ ይከታተላል፣
4. ፕሮግራሙን ለማስፈፀም የሚዘጋጀውን እቅድ ክንውን ይከታተላል፣
5. ከፕሮግራሙ የሚገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ለፖሊሲ ማሻሻያ በግበዓትነት ይጠቀማል፡፡

### ለ. የዩኒቨርስቲ አስተዳደር ቦርድ

የፕሮግራሙን አፈፃጸም የተለየ ትኩረት ሰጥቶ አፈፃፀሙን ይከታተላል

### ሐ. መምህራን (ፕሮግራሙን እንዲያስፈፅሙ የተመደቡ መምህራን)

1. የፕሮግራሙን አላማ በመረዳት ፕሮግራሙን ለማስፈጸም በተዘጋጀው ሰነድ መሰረት አስቀድሞ ዝግጅት በማድረግ የመማር ማስተማር ስራው የተሳለጠ እንዲሆን ያደርጋሉ፣
2. ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርትን ለመቀጠል የሚያስችላቸውን አስፈላጊና መሰረታዊ የሆነ የብቃት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ፈጠራ የታከለበት ሙያዊ ዕገዛ ያደርጋሉ፤
3. በተመደቡበት ክፍል ከተዘጋጀላቸው ሞጁል በዘለለ ለተማሪዎች የስነ ልቦና ድጋፍ ያደርጋሉ፣
4. የተማሪዎችን ሁለንተናዊ መሻሻል በየቀኑ ይከታተላሉ፣
5. የተማሪዎችን ውጤት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ወደ የሚመለከተው ክፍል ያስተላልፋሉ፡፡

በፕሮግራሙ ዉስጥ የታቀፉ ተማሪዎች

1. የፕሮግራሙን ዓላማ በመረዳት ዝግጅት ያደርጋሉ፣
2. ፕሮግራሙን ሲቀላቀሉ የሚደረግላቸውን ድጋፍ በበጎ ጎኑ በማየት ለፕሮግራሙ ማስፈፀሚያነት በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት ፕሮግራሙን ይከታተላሉ፣
3. በማስፈጸሚያ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ፕሮግራሙን መከታተል እና ከፕሮግራሙ በኂላ የሚዘጋጀውን ሃገራዊ ፈተና ለመፈተን ፍቃኛ እና ዝግጁ መሆን፣



የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic ... Ministry of Edu...

4. ፈተናውን ካለፉ በኋላ በሚሰጣቸው ምድባ መሰረት ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡

**ግብረ-ኃይል**

በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ የሚቋቋም ግብረ-ኃይል በሚኒስቴሩ የሚሰየም ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች ስራ ክፍሎች ከመደበኛ ስራቸው ጋር አስተሳስረው ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚደረግ ሲሆን የግብረ ኃሉ ተግባርና ኃላፊነት የሚከተለው ነው፡፡

1. የማካካሻ ፕሮግራሙ የሚመራበትን ማስፈጸሚያ ሰነድ/መመሪያ ያዘጋጃል፤ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፣
2. የሚመለከታቸው ሁሉ የፕሮግራሙን ማስፈፀሚያ ሰነድ መሰረት በማድረግ ፕሮግራሙን እንዲፈፅሙ እና እንዲያስፈፅሙ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች ስራ ክፍሎች ከመደበኛ ስራቸው ጋር አስተሳስረው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ለይቶ ይሰጣል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
4. በተቻለ መጠን ተቋማት ጋር በመድረስ የፕሮግራሙን አፈፃፀም ይከታተላል፤ ድጋፍ ያደርጋል ለሚመለከታቸው አካላት የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፡፡
5. በማካካሻ ፕሮግራሙ ላይ የተገኙ መልካም አፈጻጸሞችና ውስንነቶችን መሰረት አድርጎ ለተቋማትና ለባለድርሻዎች ግብረ-መልስ ይሰጣል፤

ሀ. በዩኒቨርስቲ ደረጃ የሚቋቋም አብይ ግብረ-ኃይል..

በዚህ ግብረ ኃይል ውስጥ የሚካተቱ የስራ ኃላፊዎች

1. ፕሬዝደንት --------------------------------ሰብሳቢ
2. አካዳሚክ ም/ፕ---------------------------ፀሃፊ
3. አስተዳደር ም/ፕ---------------------------አባል
4. የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር----አባል
5. የግቢዉ የፀጥታና ደህንነት ኃላፊ ---- አባል

ለ. የአብይ ግብረ ኃይሉ ተግባርና ኀላፊነት

1. ከትምህርት ሚኒስቴር ለፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ ተዘጋጅተው የሚላኩ የፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ ሰነዶችን እና ዕቅዶችን ተፈፃሚነታቸውን ይከታተላል፤
2. የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ለስራው በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ ክትትል ያደርጋል፤
3. የፕሮግራሙን አፈፃፀም ሪፖርት ለሚመለከተው የመንግስት አካል በየጊዜው ያቀርባል፤
4. መምህራን የፕሮግራሙን አላማ እንዲረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ያካሄዳል፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia

5. የተማሪዎቹን ውጤት የሚከታተልና ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆን ጥናት ማድረግ፣
6. የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑትን ተማሪዎች የስነ ልቦና ጉዳት የሚያደርስ መምህርም ሆነ ማንኛውም የአስተዳደር ሠራተኛ የሚዳኝበትን የውስጥ መመሪያ ያዘጋጃል፣
7. ከወጪ መጋራት ጋር የተያያዘ ተቋማዊ የአሰራር ስርዓት በአግባቡ መተግበሩን ክትትል ያደርጋል፤
8. የፕሮግራሙን አፈፃፀም በቅርበት ይከታተል በበላይነት ይመራል፣
9. የትምህርት ግብዓት በአግባቡ መሟላቱን ያረጋግጣል፣
10. የትምህርት ክፍለ ጊዜ(Course load) ክፍፍሉ ፍትሃዊ እንዲሆን ክትትል ያደርጋል፣
11. ተማሪዎቹ ወደ ተቋሙ ከመግባታቸው በፊት ለተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ የመማሪያ ክፍሎች፤ ቤተ መፃህፍት፤ ላቦራቶሪ አካባቢዎች በበቂ ሁኔታ መዘጋጀታቸዉን ያረጋግጣል፤
12. እንደ አስፈላጊነቱ ንዑሳን ግብረ ኃይሎችን ሊያቋቁም ይችላል

**ሰ. በዩኒቨርስቲ ደረጃ የሚቋቋም ቴክኒክ ግብረ-ኃይል**

በዚህ ግብረ ኃይል ውስጥ ልካተቱ የሚችሉ የስራ ኃላፊዎች

1. የአንደኛ ዓመት ፕሮግራም አስተባባሪ/ዳይሬክተር…ሰብሳቢ
2. የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር………………ፀሃፊ
3. የሬጅስትራር ዳይሬክተር……………………………አባል
4. የ "guidance and counselling" ባለሙያ………አባል
5. የግቢዉ የፀጥታና ደህንነት ኃላፊ…………………አባል
6. የክሊኒክ ኃላፊ………………………………………አባል
7. የምግብ ቤት ኃላፊ…………………………………አባል

**መ. የቴክኒክ ግብረ-ኃይሉ ተግባርና ኃላፍነት**

1. ተማሪዎቹ ወደ ተቋሙ ከገቡ በኋላ ለተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች የተማሪ ማደሪያ፤ መመገቢያ አደራሾች፤ መማሪያ ክፍሎች እና መዝናኛ አካባቢዎች በበቂ ሁኔታ መዘጋጀታቸዉን ያረጋግጣል፣
2. የግቢው ክሊኒክ በተማሪ ቁጥር በበቂ ሁኔታ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣
3. የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች የአካዳሚክ መረጃቸዉ በተለየ ሁኔታ ለብቻው እንዲያዝ ያደርጋል፣

4. በፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች የአካዳሚክ መረጃቸው በተለየ መልኩ ከተቀመጠ በኋላ ለፕሮግራሙ የተሰጠው የማካካሻ ጊዜ ሲያልቅ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ውጤቱን ያስተላልፋል፣
5. መምህራንና ሌሎች የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እና ኃላፊዎች የፕሮግራሙን ዓላማ በመረዳት ለተማሪዎች የስነ ልቦና ግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣
6. የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑትን ተማሪዎች የስነ ልቦና ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎች መመደባቸውን ያረጋግጣል፣
7. የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑትን ተማሪዎች የስነ ልቦና ድጋፍ የሚያገኙበትን ቋሚ ቢሮ ሰዓት መድቦ ተማሪዎቹ እንዲታገዙ ያደርጋል፤
8. ተማሪዎቹ ለግቢው አዲስ ከመሆናቸው የተነሳ የግቢውን ፀጥታና ደህንነት ሁኔታን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራል፣
9. በዚህ ፕሮግራም የተካተቱ ወይም እንዲያስተምሩ ክፍል የተሰጣቸው መምህራን የዚህን ፕሮግራም አላማ በደንብ እንዲረዱና ለዚህ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ በተዘጋጀው ሰነድ መሰረት መማር ማስተማር ስራውን የተሳሰጠ እንዲያደርጉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
10. የተመደቡ ተማሪዎችን የክፍል ድልድል በጊዜው አዘጋጅቶ ለተማሪዎቹ እና ለሚመለከታቸው ያሳውቃል፣
11. ተማሪዎቹ ወደ ግቢ ሲመጡ የአቀባበል ፕሮግራም ያዘጋጃል።

## 18. የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ

ይህ የማካካሻ ትምህርት ልዩ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ በተዋረድ ከፍተኛ ክትትልና ግምገማ በሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚደረግ ይሆናል። በዚህም

1. በትምህርት ሚኒስቴር የሚቋቋም ግበረ ኃይል በየወሩ ስራውን ይገመግማል፣
2. በትምህርት ሚኒስቴር የሚቋቋም ግበረ ኃይል በየሁለት ወር የአካል ምልከታ በማድረግ፣ ለሚኒስትሪው ሪፖረት ያቀርባል መሻሻል ያለባቸው ሀሳቦች ያሻሽላል፤
3. በዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዴንት የሚመራ ግብረ ኃይል በየሁለት ሳምንት የስራውን አፈጻጸም ግምገማ ያካሂዳል፣
4. በዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዴንት የሚመራ ግበረ ኃይል በየሁለት ሳምንት ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፣
5. በትምህርት ክፍል የሚመራ ግበረ ኃይል በየሳምንቱ የስራ ግመገማ ያደረጋል።



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education

## 19. የፕሮግራሙ ማጠቃለያ ፈተና

በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጅ ሲሆን ተማሪዎቹ ባሉበት ዩኒቨርስቲ የሚፈተኑ ይሆናል፡፡ የፕሮግራሙ ማጠቃለያ ፈተና በፕሮግራሙ የመጨረሻ ሳምንት በማእከል ተማሪው ከወሰዳቸው የትምህርት አይነቶች የተውጣጣ ጥያቄ ተዘጋጅቶ የሚሰጥ ሆኖ ማንኛውም በፕሮግራሙ የታቀፈ ተማሪ በማጠቃለያ ፈተና ሃምሳ ፐርሰንትና ከዚያ በላይ ማምጣት ይጠበቅበታል፡፡

## 20. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የማስፈፀሚያ ስልት በ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በሁሉም ሃገሪቱ ክልል የሃገር አቀፍ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ወስደው ለማካካሻ ፕሮግራም መንግስት የወሰነውን የመቁረጫ ነጥብ ያሟሉ ተማሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## የድርጊት መርሃ ግብር

ሰንጠረዥ 1፡- የፕሮግራሙ የድርጊት መርሃ ግብርን የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ተቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | የክንውን ጊዜ | ፈፃሚ አካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የማስፈፀሚያ ሰነድ ማዘጋጀት | ጥር | ➢ ኮሚቴው | |
| 2 | በተቋማት የመቀበል አቅም መሰረት በፕሮግራሙ የሚታቀፉ ተማሪዎችን መለየት | ጥር | ➢ ት/ት ሚኒስቴር | |
| 3 | የተማሪ ምደባ ማካሄድ | የካቲት | ➢ ት/ት ሚኒስቴር | |
| 4 | በፕሮግራሙ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠር | የካቲት | ➢ ት/ት ሚኒስቴር<br>➢ ዩኒቨርሲቲዎች | |
| 5 | ፕሮግራሞች የሚሰጥባቸውን ተቋማት መለየት | የካቲት | ➢ ት/ት ሚኒስቴር | |
| 6 | ትምህርቱን የሚሰጡ መምህራን ትኩረት የሚደረግባቸዉ ትምህርት ዓይነቶች እና ይዘት መለየት | ጥር እስከ የካቲት | ➢ ት/ት ሚኒስቴር | |
| 7 | የተማሪዎች ቅበላ ማድረግ | መጋቢት | ➢ ዩኒቨርሲቲዎች | |
| 8 | ፕሮግራሙን ማስጀመር | መጋቢት | ➢ ዩኒቨርሲቲዎች | |
| 9 | ተከታታይ የተማሪ ምዘና እንዲካሄድ ማድረግ | በተከታታይ | ➢ ዩኒቨርሲቲዎች | |
| 10 | ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | በተከታታይ | ➢ ት/ት ሚኒስቴር | |
| 11 | የማጠቃለያ ፈተና በማእከል እንዲዘጋጅ ማድረግ | ሰኔ | ➢ ት/ት ሚኒስቴር | |
| 12 | የማጠቃለያ ፈተና መስጠት | ሃምሌ | ➢ ት/ት ሚኒስቴር<br>➢ ዩኒቨርሲቲዎች | |
| 13 | የፈተና ውጤት ማሳወቅ | ነሃሴ | ➢ ት/ት ሚኒስቴር | |



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 14 | በውጤታቸው መሰረት የተማሪ ምደባ በአዲስ መልክ ማካሄድ | ነሃሴ | ➢ ት/ት ሚኒስቴር | |
| 15 | ምደባ ያገኙትን ተማሪዎች የወጪ መጋራት ሥርዓት ውስጥ ማስገባት | መስከረም | ➢ ዩኒቨርሲቲዎች | |